# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

### የእህቶች ፐሮግራም

የቤተ ክርስቲናችን የእህቶች አገልግሎት በNovember 9 ከ 3 p.m. እስከ 5 p.m. የቃል፣ የጸሎትና የህብረት ጊዜ ፕሮግራም ለህቶች ሁሉ መዘጋጀቱን በደስታ ይገልጻል። ቦታው በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ይሆናል። እህቶች ሁሉ ተጋብዛችኋል። ወንድሞች እህቶች እንዲካፈሉ እንድታበረታቱ አገልግሎቱ ያሳስባል።

### የአርብ ፐሮግራም

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

### እርስ በርስ እንተያይ

የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!



"ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ ስለ ጠላትህ፥ ጠላትንና ቂመኛን ለማጥፋት።" (መዝ. 8:2)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**October 27, 2019** | **ጥቅምት 16፣ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

**ጸሎት** ........................ የቤተ ክርስቲያን ልጆች

**አምልኮ**........................ የቤተ ክርስቲያን ልጆች

**ፕሮግራም መሪ** ............ የቤተ ክርስቲያን ልጆች

**ቃል** ............................ ወንድም ሊበን

**ማጠቃለያ** .................... የቤተ ክርስቲያን ልጆች

### የሳምንቱ ጥቅስ

"ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።"
(ምሳሌ 22:6)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንጬቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### የትውልድ ባላደራነት።

ከቤተ ክርስቲያናችን ራዕይ መካከል አንዱ "በእምነት ጠንካራ፣ በአእምሮ ደግሞ የላቁ ልጆችን ማሳደግ" ነው። ልጆቻችን በእምነት የጠነከሩ ሆነው እንዲያድጉ መትጋት አለብን። የዚህ ትጋት አቅጣጫ ደግሞ ልጆቻችን እግዚአብሔርን በግል እንዲያውቁና እንዲወዱ መርዳት ነው። ለዚህ ቁልፉ ነገር አዘውትረን ለልጆቻችን መጸለይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማርና ከቅዱሳን ልጆች ጋር ሕብረት እንዲኖራቸው ማመቻቸት ነው። እንዲሁም ልጆቻችን በእውቀትና በጥበብ ልቀት እንዲኖራቸው መቅረጽ ይገባናል።

እግዚአብሔር ቃሉን ለልጆቻችን እንድናስተምር አዟል። እግዚአብሔር ለሙሴ "ሕዝቡን በምድርም በሕይወት በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ እኔን መፍራት ይማሩ ዘንድ፥ ልጆቻቸውንም ያስተምሩ ዘንድ ቃሌን አሰማቸዋለሁ" ብሎ ተናግሮታል (ዘዳ. 4:9-10)። ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው እግዚአብሔር ቃሉን ለልጆቻችን እንድናስተምር አዟል። ይህንን ደግሞ የምናደርገው ልጆቻችን እግዚአብሔርን መፍራት ይማሩ ዘንድ ነው። እንደዚሁም እግዚአብሔር ለእስራኤል "እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው" ሲል አዟል (ዘዳ. 6፡ 6-7)። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ቃል ስለ ልጅ አስተዳደግ መመሪያ ሲሰጠን "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም" ይለናል። (ምሳሌ 22:6) ልጆቻችንን በሚሄዱበት መንገድ የምንመራብት ዋናው መንገድ ለልጆቻችን የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ነው። ልብ እንበል -- ይህ ኃላፊነት በዋናነት የቤተ ክርስቲያን ኃላፊትነት ሳይሆን የወላጅ ኃላፊነት ነው። ለልጆቻችን የእግዚአብሔር ቃል ስናስተምር ልጆቻችን እግዚአብሔርን በቃሉ ወደ ማወቅ ይመጣሉ፤ እንደ ቃሉም የሆነ የጽቅን አቋም ይይዛሉ። ለዚህ በጣም ጥሩ ማስረጃ የሚሆኑን ዳንኤልና ጓደኞቹ ናቸው። እነ ዳንኤል ወደ ባቢሎን በምርኮ ተውስደው በገጠማቸው ተግዳሮት ሁሉ ውስጥ በጽናት እግዚአብሔርን አስከብረው ለመቆም የቻሉት ከልጅነታቸው ጅምረው የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ተማሩና በቃሉ እግዚአብሔርን ስላወቁት ነው። ዮሴፍም እንደዚሁ ለገጠመው የኃጢያት ግብዣ እንቢ እንዲል ያስቻለው "በእግዚአብሔር ፊት" ይህንን እንዴት አደርጋለሁ ከሚለው እግዚአብሔርን ከማወቅ ከመጣው የጽድቅ አቋሙ የተነሳ ነው።

ልጆቻችን በአእምሮ ልቀትም ምሳሌ መሆን አለባቸው። እነ ዳንኤል በጥበብና በመረዳት የሚቋቋማቸው አልነበረም። ንጉሡ በተነጋገራቸው ጊዜ ከብላቴኖቹ ሁሉ እንደ እነ ዳንኤል ያለ አልተገኘም። በጥበብና በማስተዋል ሁሉ ከሌሎቹ ከእነርሱ ጋር ከነበሩት ሁሉ አስር እጅ በልጠው ተገኙ (ዳን. 1፡ 19-20)። ይህ ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር ለብላቴኖቹ "በትምህርትና በጥበብ ሁሉ እውቀትንና ማስተዋልን" ስለሰጣቸው ነው። (ቁ. 17) እውነት ነው እግዚአብሔር ለልጆቹ የጥበብንና የማስተዋልን መንፈስ ይሰጣል። በተጨማሪም እግዚአብሔር ስንፍናን አይወድምና ልጆቻችንን ታታሪነት ማስተማር አለብን። መጽሐፍትን ማንበብ እንዲወዱ ማድረግ አለብን።

ወገኖቼ፡- ልጆቻን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማሩ በቤታችን መጽሐፍ ቅዱስን አብረናቸው ማጥናት አለብን፤ ሁልጊዜ ስለ ልጆቻችን መጸለይ አለብን፤ በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች ላይ በትጋት እንዲሳተፉ ማድረግ አለብን። እግዚአብሔር እንደሚረዳቸውና የልቀትን መንፈስ እንደሰጣቸው ማስተማር አለብን። በስንፍና ደግሞ ወደ ኋላ እንዳይቀሩ ትጋትን ማሰነቅ አለብን። እግዚአብሔር ልጆቻችንን ይባርክ!